ቅድመ ሁኔታዎች

1. ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈፀም ማሰባቸውን እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን ለመፈፀም ከወሰኑበት ቀን ከአንድ ወር በፊት ለክብር መዝገብ ሹሙ ማስታወቅ አለባቸው። ሆኖም ይህ ድንጋጌ በሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ስርዓት የሚፈፀም ጋብቻን አይመለከትም።

2. የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄው በቀረበለት ቀን ከተጋቢዎቹ ጋር በመነጋገር ከወሰነ በኃላ በማግስቱ ጋብቻውን የሚፈፅምበትን ቀን ይገልፃል።

3. ወንዱም ሆነ ሴትዋ 18 ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ መፈፀም አይችሉም።

4. በቀጥታ የስጋ ዘመዳሞች (በወላጆችና በተወላጆች) መካከል ጋብቻ መፈፀም ክልክል ነው።

5. ወደ ጎን በሚቆጠር የስጋ ዝምድና አንድ ወንድ ከእህቱ ወይም ከአክስቱ እንዲሁም አንዲት ሴት ከወንድሟ ወይም ከአጎቷ ጋር ጋብቻ መፈፀም የተከለከለ ነው።

6. በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ጋብቻ መፈፀም የተከለከለ ነው።

7. ወደ ጎን በሚቆጠር የጋብቻ ዝምድና ባል ከሚስቱ እህት ወይም ሚስት ከባሏ ወንድም ጋር ጋብቻ መፈፀም ክልክል ነው።

8. ማንኛውም ተጋቢ አስቀድሞ በጋብቻ የተሳሰረ ከሆነ ይሄው ጋብቻ ፀንቶ በቆየበት ጊዜ ሌላ ጋብቻ አይመዘገብም።

9. ጋብቻ ሲፈፀም ሁለቱም ተጋቢዎች በአካል ቀርበው ክብር ምዝገብ ላይ መፈረም አለባቸው።

10. ተጋቢዎቹ በፍርድ ቤት እንዳይጋቡ የተከለከሉ መሆናቸው የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ የተገኘ እንደሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻውን አይመዘግብም።

11. አንዲት ሴት በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ ከላለፈ በስተቀር እንደገና ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መፈፀም አትችልም።

12. የሚፀና ጋብቻ ተፈፀመ የሚባለው ተጋቢዎቹ ለመጋባት ነፃና ሙሉ ፍቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው።

13. በሙሽራው በኩል 2 በሙሽሪት በኩል 2 በድምሩ 4 ምስክሮች መቅረብ አለባቸው።

14. ተጋቢው ስደተኛ ከሆነ የስደተኝነት እውቅና ያገኘና ከሚኖርበት አገር የፀና መኖሪያ ፈቃድ ያለው መሆን አለበት።

15. በማንኛውም ስርዓት የሚፈፀም ጋብቻ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት።

ደጋፊ ማስረጃዎች

1. ተጋቢዎች ማንነታቸውን የሚገልፅ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው

2. የተጋቢ ምስክሮች አገልግሎቱ ያላለፈበት የነዋሪነት/ ብሄራዊ መታወቂያ ወይም የስደተኝነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም ሌላ ማንነትን ሊገልፅ የሚችል ማስረጃ መቅረብ አለበት

3. ተጋቢዎች ከዚህ በፊት አግብተው የተፋቱ ከሆነ የፍቺ ምስክር ወረቀት ማስረጃ ወይም ያላገባ ማስረጃ ወረቀት ከሚኖሩበት አገርና ከትውልድ አገራቸው ማቅረብ አለባቸው

4. ከ 6 ወር ወዲህ በተመሳሳይ ጊዜ የተነሱት ሁለት ሁለት 3 በ 4 የሆነ የተጋቢዎች ፎቶግራፍ መቅረብ አለበት

5. በባህላዊ ስርዓት የተፈፀመ ጋብቻ የተጋቢዎች ምስክሮች ወይም በጋብቻ ስርዓቱ ላይ የታደመ ሰው በክብር መዝገብ ሹሙ ፊት በአካል ቀርበው ፊርማቸውን ማኖር አለባቸው

6. የተጋቢዎች የልደት ምስክር ወረቀት ካለ መቅረብ አለበት